# አሁንስ በጣም በዛ

ከታዬ ታሪኩ ጎላ
ለንደን

አሁንስ በጣም በዛ፣
የወያኔ ትዕቢት ጠነዛ።
መለስ ጨርሶ ለየለት፣
ብቻውን ማውራት ለምዶበት፣
የባጥ የቆጡን መወሻከት።

    የወያኔን አረመኔነት፣
    ዛሬም ነገም ሲመዝኑት፣
    ምንጊዜም የሞት ሞት!

ግፉን ለሚረዳ አሰላስሎ፣
ሕዝብን መስሎ ሕዝብን ወክሎ፣
የፕሮፌሰር አሥራት ሰማዕትነት፣ የብርቱካን ተጋድሎ፣
በየጊዜው የተፈፀመው ሌላው ሌላው ተቆልሎ።
ወያኔ የሠራው ግፍ በሀገራችን መሬት፣
ምህረት የሌለው ወንጀል ነው፤ ንስሃም የሌለው ሀጢያት።
አጥቦ ማስለቀቅ የማይቻል የቂም በቀል ቅርጭጭት።
ምንም መፈለግ አያስፈልግ ለወያኔ ሌላ ወንጀል፣
ከዚህ የከፋ ምን ይገኛል ጤነኛውን ሰው ከማነሁለል?

    የመለስ ነገር ያሳዝናል አውን ጤናው ጤነኛ ነው?
    የቀወሰ ይመስለኛል ንግግሩን ስመዝነው።
    በዚያ መከረኛ ሸንጎ ውስጥ እንደልቡ ሲደነፋ፣
    ምንም ሀፍረት አይሰማው የዘለፋ ቅርሻት ሲተፋ።
    በእነ አቶ ቡልቻ ደመቅሳና  አቶ ተመስገን ዘውዴ፣
    ተራ ዘለፋ ያሰማ ነበር፤ አሁን ደግሞ ባሰበት እንዴ?
    ባለፈው ሰሞን በቅርቡ፣ በሸንጎው ስበሰባ ላይ፣
    አቶ ግርማ ሰይፉን ብቸኛውን ይሕዝብ ተወካይ፣
    መለስ ራሱ እንዳለው፦ "የደርግን ስድብ በመዋስ"፣
    "አወናባጅ" ብሎታል ባልተጣፈረ ስድ ምላስ፣
    እራሱን እየቧጠጠ ጆሮና አፍንጫውን በመዳሰስ።
    ይሄ መሪ ነው እንዴ? ከአርሆ የማያንስ፣
    ለሕዝብ ክብር የሌለው፣ ያሳከመው ያጣ የቀውስ ቀውስ።

አሁን ደግሞ በዚህ ሳምንት ያሳየው ጆብደኝነት፣
ከማበድ ያለፈ ነው የሰውየው ጤንነት፣
እንዴት በመሪ ደረጃ ያንን ያክል በመፎግላት፣
በእረኞች ተራ ቋንቋ በሚሰቀጥጥ ለመስማት፣
እንደ ህፃን ልጅ አንድነትን አፉን ለማስያዝ ማስፈራራት?
ጨው አይደሉ አይሟሙ፤ አየር አይደሉ አይተንኑ፣
የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍረዳቸው፣ እነዚህ ሰዎች ምን ይሁኑ?



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ግብፅ ኢትዮጵያን ለማዳከም በሻዕቢያ ከሰለለ፣
ከኢሣይያስ ጋር መለስ እንዴት ነበር የተዋዋለ?
ያለባህር በር ያስቀራት፣ እንድትዳከም ያስገነጠለ፣
ከቶ ከመለስ የባሰ የሀገር ጠላት የት አለ?
የሠራውን የሚረሣ ከዚህስ የባሰ እብደት አለ?
የግብፅና የሻዕቢያ ተንኮል ጥርሱን ነቅሎ ያሳደገው፣
ዛሬ ዙሪያው ገደል ሲሆን ነው ሰላይነቱን የሚያውቀው?
መለስ ወደደም ጠላ የሕዝብ አመፅ ሲንጠው፣
ሰደድ እሣቱ ሲቀጣጠል ከቶ የት ይሆን የሚደርሰው?
ብዙ ሰው እኮ እግዜር ነው፣
ምንም የለም የሚሳነው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com